የእግዚአብሔር መልአክ፦ የሚመጣው መሲህ

ብሉይ ኪዳንን ስናጠና፤ የእግዚአብሔር መልአክ የተባለ አንድ አስገራሚ ገጸ-ባህሪን እንመለከታለን። ይህ አካል እግዚአብሔር ለተባለ ሌላ ማንነት መልእክተኛ ነው። ነገር ግን ራሱም እንደ አምላክና ጌታ ይናገራል። መለኮት ብቻ ሊያደርጋቸው የሚችላቸውን ነገሮች ያደርጋል፥ ይመለካል። ዛሬ ጌታ ቢፈቅድ፥ ይህ መልአክ ይመጣል የተባለው መሲህ ክርስቶስ መሆኑን ለማየት እንሞክራለን። ከዚህ በፊት እንደተነጋገርነው፥ መልአክ ማለት መልእክተኛ ማለት ነው። አሰራርን የሚገልጽ ቃል ሲሆን ለመለኮት፥ ለፍጡራን መናፍስት እና ለሰዎች ጥቅም ላይ ይውላል። የመልአኩ/መልእክተኛው ባህሪ ወይንም ህላዌ የሚታወቀው በአውዱ ነው። መጽሐፍ ቅዱስ እንደሚያስተምረው ደግሞ፥ ይህ መልእክተኛ መለኮት ነው

መልአኩ የሚመጣው መሲህ መሆኑን ያሳዩልናል ካልናቸው ቃላት መካከል፥ የመጀመሪያውን እንመልከት

(ትንቢተ ኤርምያስ ምዕራፍ 23)

5፤ እነሆ፥ *ለዳዊት* ጻድቅ *ቍጥቋጥ* የማስነሣበት ዘመን ይመጣል፥ ይላል እግዚአብሔር፥ እርሱም እንደ *ንጉሥ* ይነግሣል፥ ይከናወንለታልም፥ በምድርም ፍርድንና ጽድቅን ያደርጋል።

6፤ በዘመኑም ይሁዳ ይድናል እስራኤልም ተዘልሎ ይቀመጣል፥ የሚጠራበትም ስም። *እግዚአብሔር* ጽድቃችን ተብሎ ነው።

► ነቢዩ ኤርምያስ በመንፈስ ቅዱስ ጠንሳሽነት (ዘካ 7:12) ወደፊት ስለሚመጣው መሲህ አስደናቂ ትንቢትን ይናገራል። በመጀመሪያ አስተውሎትን የሚሻው ነገር፥ ይህ እግዚአብሔር የሚያስነሳው ሰው የሚነሳው ለዳዊት መሆኑ ነው። ይህ ሰው ለዳዊት ቤት ይነሳል። ይህ ደግሞ መሲሁ መሆኑን በግልጽ የሚያመለክት ነው። ምክንያቱም በ2 ሳሙ 7 ላይ፥ ነቢዩ ናታን ለንጉሥ ዳዊት እግዚአብሔር ከሆዱ ፍሬ በዙፋኑ ላይ እንደሚያስቀምጥለትና፤ ይህም ልጁ መንግስቱ ለዘላለም እንደሚጸና ይነግረዋል። መሲሁ በዳዊት ዙፋን ላይ የሚቀመጥ የዳዊት የስጋ ልጅ ነው። ስለዚህ በዚህ ስፍራም እግዚአብሔር ለዳዊት ጻድቅ ቁጥቋጥ አስነሳለሁ ሲል፤ ያኔ በነብዩ ናታን አማካኝነት ለንጉሱ የተናገረውን እየደገመ ነው።

ሁለተኛው፥ የዚህ ሰው ስም ቁጥቋጥ መሆኑ ነው። በመላው ብሉይ ኪዳን፥ ከመሲሁ ስሞች መካከል አንዱ "ቁጥቋጥ" እንደሆነ እንረዳለን። ለምሳሌ:- በዘካ 6 ላይ እግዚአብሔር "ቁጥቋጥ" የተባለ ሰው እንደሚበቅልና የእርሱን ቤተ-መቅደስ እንደሚሰራ ይናገራል። ለዘላለም ይነግሳል የተባለው የዳዊት ልጅም እንዲሁ ለእግዚአብሔር ቤተን እንደሚሰራ መጽሐፍ ቅዱስ ያስተምራል (2 ሳሙ 7፥13) በተጨማሪም በኤር 23 ላይ፥ ይህ ለዳዊት ይነሳል የተባለው ቁጥቋጥ እንደ ንጉሥ እንደሚገዛ ተነግሯል። በዘካ 6ም እንዲሁ፥ ይህ ቁጥቋጥ ንጉስ እንደሚሆን በግልጽ ተጽፏል። በዚህም ምክንያት ይህ ክፍል ስለማን እየተናገረ እንደሆነ እርግጠኞች መሆን እንችላለን። ስለ መሲሁ ነው

ነገር ግን በዚህ ስፍራ፥ መሲሁ በአንድ በሌላ ስያሜም ተጠርቷል። ይኸውም እግዚአብሔር (ያሕዌ) ጽድቃችን በመባል ነው። ነቢዮ፥ በቀጥታ የሚመጣውን መሲህ "እግዚአብሔር (ያህዌ)" በማለት ጠርቶታል። ይህ ከምንም በላይ መሲሁ ፍጡር እንዳልሆነ፥ ነገር ግን እግዚአብሔር እንደሆነ የሚያረጋግጥ ቃል ነው። መሲሁ እግዚአብሔር ነው። ሁለተኛው ነጥብ ደግሞ፥ ምንም እንኳ ይህ መሲህ እግዚአብሔር ቢሆንም፥ ከእግዚአብሔር በማንነት ተለይቷል። ቁ.5 ላይ እግዚአብሔር ለዳዊት አስነሳለሁ ብሎ ቃል ሲገባ እንመለከታለን። በቁ.6 ላይ ደግሞ ያ እርሱ አስነሳዋለሁ ያለለት (መሲሁ) እግዚአብሔር ተብሎ ሲጠራ እንመለከታለን። መሲሁም፥ እርሱን አስነሳዋለሁ (ማስነሳት ማለት በስጋ መላክ ማለት ነው ሮሜ 8:3 1ዮሐ 4:14 1 ዮሐ 4:9 ሐዋ 13:23) ያለውም፥ ሁለቱም እግዚአብሔር ተብለው ሲጠሩ እንመለከታለን። (ኤር 23:7) ይህ የማንነት ሁለትነትን በግልጽ የሚያሳይ ነው

የክርስቶስን ጌትነት መቃወም የሚሹ ወገኖች ግን ኤር 23:5-6 የመሲሁን አምላክነት አያሳይም ይላሉ። ለዚህ ሀሰት ዋና መከራከሪያቸው ኤር 33:16 ነው።

" *በዚያም ዘመን* ይሁዳ ይድናል ኢየሩሳሌምም ተዘልላ ትቀመጣለች፤ የምትጠራበትም ስም። እግዚአብሔር ጽድቃችን ተብሎ ነው። " (ትንቢተ ኤርምያስ 33:16)

"በዚያ ስፍራ ላይ ኢየሩሳሌም "እግዚአብሔር ጽድቃችን" ተብላ ትጠራለች ይላል። እግዚአብሔር ጽድቃችን ተብሎ መጠራት አምላክ የሚያደርግ ከሆነ፥ ኢየሩሳሌምም አምላክ ናት ሊባል ስለሆነ ኤር 23:5-6 የመሲሁን አምላክነት አያሳይም" ይላሉ። ነገር ግን ይህ ሀሰት ነው

ምክንያቱም መጽሐፍ ቅዱስን ስናጠና፤ ከተማ በገዢዋ ስም ልትጠራ እንደምትችል እንረዳለን። ለምሳሌ፦

" ቃየንም ሚስቱን አወቀ፤ ፀነሰችም፥ ሄኖሕንም ወለደች። *ከተማም ሠራ*፥ የከተማይቱንም *ስም* በልጁ ስም ሄኖሕ አላት።"

(ኦሪት ዘፍጥረት 4:17)

ሄኖሕ የተጸውዖ ስም ሲሆን፥ በዚህ ስያሜ የሚጠራው ሰው ነው። ከተማይቱ ሄኖሕ የተባለችው በሰውየው ስም በመጠራቷ እንጂ ስሙ የሰው ስም ነው። ኢየሩሳሌምም መሲሁ በሚገዛት ዘመን እግዚአብሔር ጽድቃችን ተብላ የምትጠራው፤ በገዢዋ በመሲሁ ስም ስለምትጠራ እንጂ ስሙ የእግዚአብሔር ስም ነው። መሲሁ እግዚአብሔር በመሆኑ ምክንያት የጠራበት ስም ነው። ይህንንም ከራሱ ከኤርምያስ 33:16 አውድ እንረዳለን

" በዚያም ዘመን በዚያም ጊዜ *ለዳዊት* የጽድቅን ቍጥቋጥ አበቅልለታለሁ፤ እርሱም ፍርድንና ጽድቅን በምድር ያደርጋል። "

(ትንቢተ ኤርምያስ 33:15)

ከላይ በቁ.16 ላይ እንደተመለከትነው፥ ኢየሩሳሌም "እግዚአብሔር ጽድቃችን" ተብላ የምትጠራው "በዚያ ዘመን" ነው ይላል። ያ ዘመን የቱ ነው? ብለን ስንጠይቅ መልሱን በቁ.15 ላይ እናገኘዋለን። ለዳዊት ቁጥቋጥን የሚያበቅልበት ዘመን ነው። እግዚአብሔር ለዳዊት ቁጥቋጥን በሚያበቅልበት ዘመን ኢየሩሳሌም "እግዚአብሔር ጽድቃችን" ተብላ ትጠራለች። ይህ ቁጥቋጥም በምድር ሁሉ ላይ ፍርድንና ጽድቅን ያደርጋል። ከላይ በብዙ ማስረጃዎች እንዳረጋገጥነው፥ ይህ ቁጥቋጥ መሲሁ ነው። እርሱ ነው በዳዊት ዙፋን ላይ የሚቀመጠው (ኢሳ 9:6-7 2 ሳሙ 7:16 ኢሳ 16:5)

ለዚህ ነው ኢየሩሳሌም በዚያ ዘመን እግዚአብሔር ጽድቃችን ተብላ የምትጠራው። እግዚአብሔር ለዳዊት የሚያስነሳው መሲሁ ስለሚገዛት። መሲሁ እግዚአብሔር ነው፥ በዳዊት ዙፋን ላይ ተቀምጦ ከተማይቱን የሚገዛውም እርሱ ነው። በዚህም ምክንያት ከተማይቱ "እግዚአብሔር ጽድቃችን" ተብላ ትጠራለች። እንጂ "እግዚአብሔር ጽድቃችን" የሚለው ስያሜ በትክክል አምላክነትን የሚያሳይ ነው። መሲሁም በዚህ ስያሜ መጠራቱ እግዚአብሔር መሆኑን በማያሻማ መልኩ ያሳያል

➢ ታዲያ ኤር 23:5-6 መሲሁ የእግዚአብሔር መልአክ መሆኑን የሚያሳየው እንዴት ነው?

ይህ ቃል፥ የሚመጣው መሲህ የእግዚአብሔር መልአክ መሆኑን በግልጽ ያሳያል። ምክንያቱም አንደኛ፥ የእግዚአብሔር መልአክ ከእግዚአብሔር የተለየ ማንነት ቢሆንም "እግዚአብሔር/ያሕዌ" ተብሎ ተጠርቷል (ዘካ 3:2 መሳ 6:16 ዘፍ 16:10-13 ኢያ 5:14-15-6:2) ልክ መሲሁ እንደተባለው ማለት ነው። ሲቀጥል መጽሐፈ ኤርምያስን ስናጠና፥ እግዚአብሔር ስለ አንድ ጥንታዊ ክስተት ሲናገር እንመለከታለን።

" ሰዶምንና ገሞራን በአጠገባቸውም የነበሩትን ከተሞች *እግዚአብሔር* እንደ ገለበጣቸው፥ ይላል *እግዚአብሔር* እንዲሁ ሰው በዚያ አይቀመጥም የሰውም ልጅ አይኖርባትም። "

(ትንቢተ ኤርምያስ 50:40)

► በዚህ ስፍራ እግዚአብሔር በከለዳውያን (ወይም ባቢሎናውያን) ላይ ስለሚደርሰው ፍርድ ሲናገር እንመለከታለን። የሚመጣባቸውን ፍርድ ሲናገር ከሰዶምና ከገሞራ ጋር ያነጻጽራቸዋል። ሰዶምና ገሞራ እንደተገለበጡ ሁሉ፥ ከለዳውያንም ይገለበጣሉ። ይህ አይነቱ ንጽጽር እና ምልከታ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የተለመደ ነው። ነገር ግን በዚህ

ቃል ውስጥ አንድ እንግዳ ነገር እንመለከታለን። እግዚአብሔር "ሰዶምና ገሞራን እንደገለበጥኳቸው" አላለም። በሶስተኛ መደብ "እግዚአብሔር እንደገለበጣቸው" ነው ያለው

ለምንድነው እግዚአብሔር ሰዶምና ገሞራን ያጠፋቸው ሌላ አካል ይመስል በዚህ መልኩ የሚናገረው? እግዚአብሔር በሶስተኛ መደብ፥ ስም ጠቅሶ "እግዚአብሔር እንደገለበጣቸው" ብሎ የተናገረበት ምክንያት፥ ሰዶምና ገሞራን ያጠፋ ሁለተኛ መለኮታዊ አካል በመኖሩ ነው። ከእርሱ በማንነት የተለየ፥ ነገር ግን እግዚአብሔር የሆነ። ያንን ተግባር የፈጸመው እርሱ ነው እያለ ነውና። አንዳንድ የተሳሳቱ ወገኖች፥ እግዚአብሔር "እግዚአብሔር እንደገለበጣቸው" ብሎ በሶስተኛ መደብ መናገሩ ሁለተኛ መለኮታዊ አካል መኖሩን አያሳይም ይላሉ። የሰዋሰው አጠቃቀም እንጂ ሁለተኛ ማንነትን አያመለክትም ሲሉ ይደመጣሉ።

► ይህ ግን ፈጽሞ ስህተት ነው። ምክንያቱም ዋናውን የሰዶምና የገሞራን የጥፋት ታሪክ ስናነብ፤ ለምን እግዚአብሔር በነብዩ ኤርምያስ አማካኝነት እንደዚያ ብሎ እንደተናገረ ይገባናል። ዋናውን የሰዶምና የገሞራን የጥፋት ታሪክ ከዘፍ 18 እስከ 19 ተዘግቦ እናገኘዋለን። አስፈላጊ የሆኑ ነጥቦችን እንመልከት

" በቀትርም ጊዜ እርሱ በድንኳኑ ደጃፍ ተቀምጦ ሳለ *እግዚአብሔር* በመምሬ የአድባር ዛፍ ተገለጠለት። "

(ኦሪት ዘፍጥረት 18:1)

በዚህ ስፍራ አብርሃም በቤቱ ደጃፍ ተቀምጦ ሳለ፥ እግዚአብሔር እንደተገለጠለት መጽሐፍ ቅዱስ ይነግረናል። ቀና ብሎ ሲመለከት ሶስት ሰዎች በፊቱ ቆመው ያያል (ቁ.2) ከዚያም ፈጥኖ ይነሳና እነርሱን ማስተናገድ ይጀምራል። እግራቸውን ያጥባል፤ እህልም ያቀርብላቸዋል። መላው ታሪኩን ስንመለከት፥ ከሶስቱ ሰዎች አንዱ እግዚአብሔር መሆኑን እንረዳለን። በቀጥታ እግዚአብሔር ተብሎ ተጠርቷል (ዘፍ 18:13) እንደ እግዚአብሔርም ይናገራል (ዘፍ 18:10)

➢ መጽሐፍ ቅዱሳችንን ስናጠና፤ በሰው አምሳል ተገልጦ ያሕዌ የሚባለው፥ እንደ እግዚአብሔር የሚናገረው፥ የሚመለከው፤ የእግዚአብሔር መልአክ መሆኑን እንረዳለን። መጽሐፍ ቅዱስም ለዚህ ሀቅ እጅግ ብዙ ማስረጃዎችን ይሰጣል። ለምሳሌ ያህል፦ መልአኩ በሰው አምሳል ተገልጦ ከያዕቆብ ጋር በታገለ ግዜ ያሕዌ ተብሎ ተጠርቷል (ዘፍ 32:9/ሆሴ 12:6) ለኢያሱ በተገለጠ ግዜ ያሕዌ ተብሏል (ኢያ 6:2) ለጌዴዎን ተገልጦ መስዋዕትን በተቀበለ ግዜ ያሕዌ ተብሏል (መሳ 6:14) ለአጋር በውሃው ምንጭ አጠገብ በተገለጠ ግዜ ያህዌ ተብሏል (ዘፍ 16:13) ስለዚህ በዘፍ 18፥ ለአብርሃም በሰው አምሳል የተገለጠው እግዚአብሔር ማን እንደሆነ እርግጠኞች መሆን እንችላለን፥ መልአኩ ነው።

ሲቀጥል፥ በዘፍ 18:20-21 ላይ እግዚአብሔር የሰዶምና ገሞራ ሀጢያት በመብዛቱ ወደ እነሱ እንደሚወርድ ለአብርሃም ይነግረዋል። ከዚያም አብረውት የነበሩት ሁለቱ ሰዎች ሲሄዱ፥ እግዚአብሔር ከአብርሃም ጋር ይቀርና መነጋገር ይጀምራሉ። አብርሃምም ለከተማይቱ ምልጃን በእግዚአብሔር ፊት ያቀርባል። እርሱም በከተማይቱ አስር ጻድቃን እንኳ ቢኖሩ ለነርሱ ሲል ከተማይቱን እንደሚተዋት ቃል ይገባለታል። ንግግራቸውን ከጨረሱ በኋላ እግዚአብሔር ይሄዳል (ዘፍ 18:33) በዘፍ 18:20-21 መሰረት፥ እግዚአብሔር ሄደ ሲል ወደ ሰዶምና ገሞራ ነው። ወደ ሰዶምና ወደ ገሞራ ሄደ

➢ አስተውሉ! ወደ ሰዶምና ገሞራ እሄዳለሁ ብሎ ለአብርሃም ቃል የገባለት ያ በሰው አምሳል የተገለጠለት አምላክ ነው። እርሱ ነው ከተሞቹን ለማጥፋት የሄደው። ይህም ሀቅ በዘፍ 19:24 ተረጋግጧል። በዚያ ስፍራ ላይ፥ እግዚአብሔርም ከእግዚአብሔር ዘንድ ከሰማይ እሳትንና ዲንን በከተሞቹ ላይ አዘነበ ይላል። ይህ በራሱ ግልጽ የሆነ ቃል ነው። አንዱ አካል ከሌላኛው ዘንድ እሳትን አዘነበ። በመጀመሪያው አንቀጽ "እግዚአብሔር" ሲል በሰው አምሳል የተገለጠውን ሲሆን፥ በሁለተኛው ደግሞ ከቶውኑ ያልታየውን ማንነት ነው። ለአብርሃም የተገለጠው አካል የማይታየው አካል ካለበት ከሰማይ እሳትን አዘነበ። በግልጽ ሁለት መለኮታዊ አካላትን የሚያሳይ ታሪክ ነው

ከላይ በብዙ ማስረጃዎች ለማሳየት እንደሞከርነው፥ በሰው አምሳል ተገልጦ እግዚአብሔር ተብሎ የሚጠራው መልአኩ ነው። ለአብርሃምም ተገልጦ ሰዶምና ገምራን ያጠፋው እግዚአብሔር እርሱ ነው። ለዚያም ነው እግዚአብሔር በኤር 50:40 እና በሌሎች ተጓዳኝ አንቀጾች (ኢሳ 13:19 አሞ 4:11) በሶስተኛ መደብ "እግዚአብሔር እንደገለበጣቸው"

በማለት የሚናገረው። ምክንያቱም እያወራ ያለው ስለ መልአኩ ነውና። መልአኩን ነው እግዚአብሔር በማለት የሚጠራው። ከእግዚአብሔር ዘንድ እሳትና ዲንን አዝንቦ ያጠፋቸው እርሱ ነው። እግዚአብሔር መልአኩን በተደጋጋሚ "እግዚአብሔር" በማለት ጠርቶታል (ሆሴ 12:5-6 ዘጽ 24:1 ዘጽ 23:25 ዘፍ 35:1) ስለዚህ በኤር 50:40 እና በተጓዳኝ አንቀጾቹ እርሱን "እግዚአብሔር" ብሎ መጥራቱ አዲስ አይሆንም።

ሌላው ነጥብ፤ በኤር 50:40 እና በሌሎቹ አንቀጾች ላይ እግዚአብሔር በሶስተኛ መደብ መናገሩ ተራ የሰዋስው አጠቃቀም ሊሆን አይችልም። ምክንያቱም ይህ ቃል እያስታወሰ ያለው በሰው አምሳል የተገለጠው አካል እንዴት ካልታየው አካል ዘንዶ እሳትን አዝንቦ እንዳጠፋቸው ነው። ሰዋሰው አይደለም። ራሱን የቻለ አውዳዊ እና ታሪካዊ አፈታትን የሚሻ ቃል ነውና። ከላይ በማስረጃ ለማየት እንደሞከርነው፥ በሰው አምሳል ተገልጦ ያሕዌ ወይንም ኤሎሂም የሚባለው መልአኩ ነው። (ዘጽ 24:10 ዘጽ 24:1 ዘጽ 23:21 ዘጽ 3:2/ዘጽ 3:15)

ይህ ሁሉ እንዴት የሚመጣው መሲህ የእግዚአብሔር መልአክ መሆኑን ያሳያል?

ይህ ሀቅ፥ የሚመጣው መሲህ እርሱ መሆኑን በግልጽ ያሳያል። ምክንያቱም በመላው ትንቢተ ኤርምያስ ውስጥ ከእግዚአብሔር በማንነት ተለይቶ (ወይንም እንደ ሁለተኛ አካል ተገልጾ) እግዚአብሔር ተብሎ የተጠራው መልአኩ ነው። መልአኩ ነው በሰው አምሳል የተገለጠው። መልአኩን ነው እግዚአብሔር በሶስተኛ መደብ የጠራው። ይህ የተለየ ማንነት መሆኑን በግልጽ የሚያሳይ ነው። የተለየ ማንነት ቢሆንም፥ እግዚአብሔር ተብሎ ተጠርቷል (ኤር 50:40)

ልክ እንደ መልአኩ፥ መሲሁ ከእግዚአብሔር በማንነት ቢለይም እንኳ (አስነሺ/ላኪና ተላኪ ናቸው) እግዚአብሔር ተብሎ ተጠርቷል። ይህ በግልጽ የሚመጣው መሲህ፥ ያ ሰዶምና ገሞራን ያጠፋው መልአክ መሆኑን ያሳያል። በመጽሐፈ ኤርምያስ ከእርሱ በቀር ከእግዚአብሔር በማንነት ተለይቶ ሳለ "እግዚአብሔር" ተብሎ የተጠራ የለምና። በዚህም ምክንያት፥ ኤር 23:5-6 እና ኤር 50:40 የእግዚአብሔር መልአክ የሚመጣው መሲህ መሆኑን የሚያረጋግጡ ቃላት መሆናቸውን እናረጋግጣለን።

➤ መደምደሚያ

የእግዚአብሔር መልአክ እግዚአብሔር ነው (ዘፍ 31:11-13)። ከአምላክነቱ ባሻገር የእግዚአብሔርም ልጅ ነው (ዳን 3:25 ምሳ 30:4) እርሱ፥ በቅድመ ስጋዌ ዘመኑ የነበረው ኢየሱስ ክርስቶስ ነው። ኤር 23:5-6 እና ኤር 50:40ም ለዚህ የማይታበል ሀቅ ማስረጃዎች ናቸው።

ጌታ ይርዳን!